Paid Leave Oregon

# በግል ስራ የሚተዳደር
## የማረጋገጫ ዝርዝር

ይህንን የማረጋገጫ ዝርዝር በግል ስራ እንደሚተዳደር ሰው ለPaid Leave Oregon ሽፋን ለመምረጥ ለመዘጋጀት ይጠቀሙበት። የበለጠ መረጃ በ paidleave.oregon.gov ላይ ያግኙ።

Paid Leave Oregon በ Oregon የሚገኙ ሰራተኞች እና የግል ስራ የሚሰሩ ሰዎች ለቤተሰብ፣ ለህክምና እና ደህንነቱ ለተጠበቀ እረፍት ክፍያ ያለው የእረፍት ጊዜ ይፈቅድላቸዋል።

የግል ስራ የሚሰሩ ከሆነ፣ በPaid Leave Oregon ስር ወድያውኑ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሽፋን አያገኙም።

የሚከተለው ከሆነ ሽፋን መምረጥ ይችላሉ፡-

- ☐ ስራዎ በኦሪጎን ውስጥ ነው **እና**
- ☐ ከማመልከትዎ በፊት ባለው የግብር አመት ከግል ስራ በኦሪጎን የተጣራ ገቢ ቢያንስ $1,000 (ከወጪዎ በኋላ ያለ ገቢ) ካገኙ።

## በግል-ስራ የምተዳደር ነኝ?

Paid Leave Oregon እንዴት በአጠቃላይ የግል ስራ ምን እንደሆነ እንዴት እንደሚተረጉመው እነሆ፡-

- ☐ ለተወሰነ አሰሪ ከመስራት ይልቅ ለንግድ ሥራዎ የሚሰሩ ከሆነ **እና**
- ☐ እርስዎ ከንግድ ሥራዎ የሚያገኟቸውን ትርፎች እንደ የግል ስራ የሚተዳደር ሰው ገቢ አድርገው በግብርዎ ላይ ሪፖርት ካደረጉ።

## ይዘጋጁ

በማንኛውም ሰዓት የPaid Leave Oregon ሽፋን መምረጥ ይችላሉ። በFrances Online ላይ መለያን በመፍጠር ይጀምራሉ። ማስታወስ ያለብዎ አንዳንድ ነገሮች እነሆ፡-

- ☐ በFrances Online ላይ በግል ስራ እንደሚተዳደር ሰው የአሰሪ መለያይፈጥራሉ።
- ☐ የPaid Leave Oregon ሽፋንን ሲመረጡ፣ እርስዎ ቢያንስ ለሶስት አመታት አስተዋጽኦዎችን ለመክፈል ይስማማሉ።
- ☐ ሽፋን ለማግኘት ሲያመለክቱ በጣም ቅርብ ለሆነው ግብር የኦሪገን እና የፌዴራል ግላዊ የገቢ ግብር ተመላሾችን የተሟላ ቅጂ ማቅረብ ያስፈልግዎታል።

## Paid Leave Oregon እንዴት መምረጥ እንደሚቻል

**ደረጃ 1**፡- ሰነዶችዎን ይሰብስቡ

ከማመልከትዎ በፊት የሚከተሉት ሰነዶች እና መረጃ ዝግጁ ማድረግ ያስፈልግዎታል፤

- ☐ በጣም የቅርብ ከሆነው የግብር ዓመት የኦሪገን እና የፌዴራክ ግላዊ የገቢ ግብር ተመላሾች።
  - ይህ የሚያካትተው እንደ Schedule C፣ Schedule E ወይም Schedule F ያሉ ማናቸውም ተዛማጅ ሰነዶችን ነው። እንዲሁም በማመልከቻዎ ላይ የተሰጠዎትን ማንኛውንም Schedule K-1 ማካተት አለብዎት።
  - ቅጂዎች ከሌሉዎት፣ ከOregon Department of Revenue እና Internal Revenue Service ሊጠይቁ ይችላሉ።
- ☐ ካለፈው የግብር አመት ከግል ስራ (ከወጪዎችዎ በኋላ ያለ ገቢ) የሚመጣ የተጣራ ገቢ።

**ደረጃ 2**፡- በግል ስራ እንደሚተዳደር በFrances Online ላይ የአሰሪ መለያ ይፍጠሩ።

**ደረጃ 3፡-** በራስ ስራ ለሚሰራ የሽፋን

አጠቃቀም Frances Online ላይ በማመልከት ለሚከፈልበት የእረፍት ሽፋን ያመልክቱ።

**ደረጃ 4**፡- በእያንዳንዱ ሩብ አመት መዋጮዎችን ይክፈሉ

እኛ የእርስዎን ማመልከቻ ከፈቀድን በኋላ፣ የOregon Employment Department
በሩብ አመት መክፈል ያለበትን የመዋጮ መጠን የክፍያ ኩፖኖች ይልክልዎታል። የግል ስራ የሚሰሩ ሰዎች የመዋጮዎችን የሰራተኛ ድርሻ ይከፍላሉ፣ ይህም 60% ከ1% የመዋጮ ተመን ነው። ለ ዓመት ያለውን የእርስዎን የመዋጮ መጠን ወደ አራት የሩብ አመት ክፍያዎች እንከፋፍላለን።

መጠኑን በFrances Online ላይ ይክፈሉ።

**ደረጃ 5፡-** ዓመታዊ የገቢ ማረጋገጫ

በየዓመቱ እስከ ኤፕሪል 30 ድረስ (ወይም እስከ ኦክቶበር 30 ድረስ በቅጥያ የግብር ተመላሽዎን ካቀረቡ)፣
የእርስዎን የኦሪገን እና የፌዴራል የግል ገቢ ግብር ተመላሾች ቅጂን ለOED ማቅረብ አለብዎት። በእርስዎ Frances Online መለያ ላይ እነዚህን ሰነዶች ሊልኩልን ይችላሉ።